# ልባዊ ሰላምታችንን እናስቀድማለን

በቅድሚያ እዚህ ታላቅ ዝግጅት ላይ መድረስ በመቻላችን የተሰማንን የጋለ ልባዊ ደስታ እንገልጻለን፡፡

ከሁሉ አስቀድመን ለአራት አስርተ አመታት አራት አመት ብቻ የቀረውን ይህን የትግል ጉዞ ሂደት በዐይነ ህሊናችሁ እንድትዳስሱት በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

የኢትዮጵያን ህዝብ ከተጫነበት የግፍ አገዛዝ ቀንበር ታግሎ ነጻነቱን እንዲዋጅ ምን መደረግ አለበት ለሚለው ጥያቄ ምላሹ የድርጅት አስፈላጊነት ይደር ይዋል የማይሉት እንደሆነ ታመነበት፡፡ይህ እምነት ኢህአፓን ጸነሰ፡፡ ከዚያም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ ፈር ቀዳጅ የሆነውን ኢህአፓን ወለደ፡፡ ኢህአፓ በተወለደበት ወቅት ፈላጭ ቀራጩ ዘውድ አገዛዝ ቃሬዛ ላይ ነበር፡፡ ህዝቡን ሳያደራጅና የፖለቲካ ፕሮገራሙን በስፋት ሳያስራጭ እንደዚያ በፍጥነት ይቀጣጠላል ተብሎ ያልተጠበቀው ህዝባዊ አመጽ በአገሪቱ ተያያዘ፡፡ ህዝቡ በስፋትና በጠነከረ መልኩ አለመደራጀቱ ለወታደራዊ አረመኔ ኃይል የግፍ አገዛዝ ተዳረገ፡፡ የወታደሮቹ ኃይል የህዝቡን አመጽ ርካብ አድርጎ ዙፋኑ ላይ ፊጥ አለ፡፡ የኢህአፓም መሪር ታሪክ ከዚያ እስከዚህ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ የኢህአፓን ከመኮንኖቹ ፈላጭ ቆራጭ መንግስት ጋር ተጋድሎ ለመዘከር ጊዜ መሻማት እንደሚሆን ይሰማናል፡፡ ነገር ግን የሚከበረው የኢህአፓ እድሜ ነውና እድሜው ደግሞ የበረከተው ልጆቹ በአጎረፉት ደም በከሰከሱለት አጥንት ነውና ልንዘክራቸው የግድ ይለናል፡፡ ኢህ አፓዎች ላይ እኒያ ግፈኛ መኮንኖችና ለነሱ ያደሩ ባንዳ ምሁር ተብዬዎችና ቦዘኔዎች ያደረሱት እጅግ በጣም ዘግናኝ ሰቆቃ የጣሊያን ፋሽስቶች ካደረሱት ባይበልጥ አይተናነስም፡፡ እኛም ታሪካችን ነውና ሳንዘክረው ሳነነሳው አናልፍም፡፡ ሴት እህቶቻችን ከአራት እስከ ስድስት በሚደርሱ መርምሪ በሚባሉ ገራፊዎች ተደፍረዋል፡፡ ልብ በሉ እህቶቻችን እናቶቻችን በአንክሮ በተዘክሮ ስሙን ወድም አባቶቻችን እህቶቻችን ብልት ውስጥ የጋለ ብርት በመጨመር አሰቃዩ ስቃይ ሰቆቃወ ገሀነም ፈጽመውባቸዋል፡፡ የእህቶቻችንን ለምለም ከንፈሮች በሲጋራ እሳት አንፍረዋቸዋል፡፡ የወንድም እህቶቻችንን የእግር ጣቶች በወፌ ኢላላ እግር ተወርች በማሰር ሙሉ በሙሉ አርግፈዋቸዋል፡፡ ጥርሶቻቸውንና ጥፍሮቻቸውን በፒንሳ ነቅለዋል፡፡ ጀርባቸውን በፈላ ዘይት አንፍረዋል፡፡ ሰውነታቸውን በፕላስቲክ ገምድ በማሰርና በጉማጅ አጠና በመቀጥቀጥ ውስጥ አካላቸው ተልቶ በትሉ ሰቆቃወ እም ሰቆቃትን እነዲሰቃዩ አድርገዋል፡፡ የወንድሞቻችንና የእህቶቻችንን ዐይኖች አውጥተዋል፡፡ እጅግ በጣም የቀዘቀዘ ውሀ እየነከሩ ገርፈዋቸዋል፡፡ በኤክተሪክ አሰቃየተዋቸዋል፡፡ በሽቦ በማነቅ እያሰቃዩ ገድለዋቸዋል፡፡ ከነነፍሳቸው ሳይሞቱ የጅምላ ጉድጓድ ከተው ቀብረዋቸዋል፡፡ ባልን አስረው ሚስትንና ልጅን ደፍረዋል፡፡ ወንድምን አስረው እህትን ደፍረዋል፡፡ ልጅን አስረው እናትን ደፍረዋል፡፡ በሌላ አንጻርም የኢህአፓ ሠራዊት ኢህአሠ የትጥቅ ትግል በጀመረበት ከወታደራዊው መንግስት ያልተናነሰ ግፍ ተፈጽሞበታል፡፡ ከላይ የተጠከሱ ግፎችን እንዳለ በወያኔና በሻዕብያ የተፈጠሙ ሲሆን ብዙዎችን በጥይት እየደበደቡ አሰቃይተው ገድለዋል፡፡ ከነህይወታቸው ለአውሬ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ሁሉ ግፍ ይህ ሁሉ መከራ ይህ ሁሉ ሰቆቃ የተፈጸመበት ኢህአፓ ጸገየ አበበ እንጂ አልጠወለገም፡፡ እንደጠላቶቹ ምኞትም አልረገፈም፡፡ እዚህ ለይ እንዳናልፈው የግድ የሚለን ግዝፍ የነሳ ም ጸትን ለማንሳት  እንወዳለን፡፡ ዛሬ በየ መድረኩ ለዴሞክራሲ ቆመናል የሚሉ የዚያኔ ይህን ሁሉ ግፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ፈታሚና አስፈጻሚ የነበሩ በአደባባይ ምንም ንስሀ ያልገቡ የጸጸት ድምጽ ያላሰሙና ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል በተግባር እየጎዱና እየተፈታተኑ ያሉትን ያየን ልባችን እየቆሰለ ነው፡፡ ለዘህም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ላይ የፈጸሙት ደባ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

ኢህአፓ ሰላሳ ስድስት አመታት መጓዙን ስናስብ ልናውቀው የሚገባን ቋጥኝ ጉዳይ ለኢህአፓ በአይበገሬነትና በቆራጥነት የቃል ኪዳን ምላሱን ሳያጥፍ ቃሉን ሳይሰብር የመቀጠሉ ምስጢር የኢህአፓ ምትሀቱ ነው፡፡ ኢህአፓ ይህን ሁሉ ዘመን በትግል የተጓዘው የእግር ሹራብና የጫማ ጭብል በማጥለቅ ሳይሆን በባዶ እግሩ ነው፡፡የኢህአፓ ምትሀቱ  በባዶ እግሩ መጓዙ ነው፡፡ በዚህ ሳቢያም በየጉዞው ምዕራፍ እግሩ በእንቅፋትና በረሙጫ ቆስሏል፡፡ ዛሬም ቆስሏል፡፡ ኢህአፓ በገሀድ ከተፋለሙትና ከሚፋለሙት ጠላቶቹ ባልተናነሰ በየትግል ምዕራፉ በጠላት በሚገዙ ባንዳዎች ተጠቅቷል፡፡ እነዚህ ከውስጡ የሚወጡ ጠላቶቹ በጊዜ ይለያዩ እንጂ ጉዟቸው አንድ ነው፡፡ ሁሉም ከኢትዮጵያ ህዝብ በስተጀርባ ኢህአፓ የአልተወለደበትንና ያላደገበትን ባእድ የአጎብዳጂነት ባህርይ ተቀብሎ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት ይጎናበስ የሚል ሀሳብን ይጋራሉ፡፡ ኢህአፓ እንደሌሎች የዴሞክራሲ ጭምብልን እንዳጠለቁ ድርጅቶች አይደለምና ኢህአፓ በህዝብ ጀርባ የሚደረግ ጉዞን ይጸናወታል፡፡ አምሮም ይቃወማል፡፡ ይታገላል፡፡ ከላይ ዐይነ ህሊናችሁን ወርወር አርጋችሁ አንድታዩት በሞከርነው መሰረተ የኢህአፓ መሰረቱ ዛሬም ድረስ እንዷለቱ ያልበረደው የእነዚያ እህት ወንድሞቻችን በገጠር በከተማው የፈሰሰው ደም ሲሆን የኢህአፓ ግድግዳም የተገነባው በለምለሙ ሥጋቸውና አጥንታቸው ነው፡፡ የኢህአፓ ጥንካሬ ምስጢሩ ሌላ ሳይሆን ድርና ማጉ ደምና አጥንት በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ያኔም ዛሬም ወደፊትም ቋሚ የኢህአፓ የማእዘን ደንጊያ ነው፡፡

ከዚህ ጋር መነሳት ያለበት ጉዳይ ኢህአፓ ሲነሳ ሁሌም ደማችንን ያፈሰስንላት ሥጋችንን የቆረስንላት አጥንታችንን የከሰከስነላት አገራችን ኢትዮጵያና ጉስቁሉና ምዝብሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይነጣጠሉ መነሳታቸው የግድ ነው፡፡ ለዚህም ነው የኢህአፓ ጥቅም የኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም የኢህአፓ ድል የኢተዮጵያ ህዝብ ድል የኢህአፓ ኩራትና ክብር የአገራችን የኢትዮጵያ ሞገስ የሚሆነው፡፡ ኢህአፓ በሰላሳ ስድስት አመታት የትግል ጉዞው በየታሪክ ምዕራፉ በርካታ ድሎችን ተቀዳጅቷል፡፡ ከማንኛውም ድርጅት በበለጠና በቀለጠፈ ሁኔታ የህዝብ ጥያቄዎችን እየተነተነ ማስተጋባቱ አይበገሬ የህዝብ አለኝታነቱን አስመስክሯል፡፡ በዚህም ወዳጅ የሚያውቀው ጠላት የማይክደው የማይሻር የህዝብ ፍቅርን አትርፏል፡፡ ይህ ደግሞ የኢህአፓ ሀብቱ ጸጋው ነው፡፡ ኢህአፓ ከዚህ ሌላ ሀብት የለውም፡፡ በዚህ ኢህአፓ በደሙና በአጥንቱ በዋጀው የህዝብ ፍቅር ጠላቶቹ ሁሌም ይባንናሉ፡፡ ይርዳሉ፡፡ ኢህአፓ ፍቅር፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍቅር፡፡

ኢህአፓ የዛሬ ሰላሳ ስድስት አመት አንግቦ የታገለላቸው ጥያቄዎች ዛሬም ተግባራዊ ምላሽ ይሻሉ፡፡ ዛሬም ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች እንደተረገጡ ነው፡፡ ዛሬም የወያኔ መሪዎች አገርንና ህዝብን እየመዘበሩና በገሀድ እየዘረፉ በህዝብ ረሀብ ጠኔ ላይ ከብረዋል፡፡ ዛሬም ሀሳብን በነጻ መግለጽ መሰበሰብ መደራጀት ሥራ በአድማ ማቆም የተከለከለ ነው፡፡ ዛሬ የዘር ከፋፍለህ ግዛ አባዜን በማስፈን የጥላቻ መርዝ በመንዛት ህዝቡ ርስ በእርሱ ደም እንዲፋሰስ ተደርጓል፡፡ በሀይማኖት መሀል መቆራቆስ በመፍጠር የብዙ ሰው ህይወት አልፏል፡፡ የጸሎት ቤቶች ፈርሰዋል፡፡ ዛሬም ሠራተኞች ከሥራ ገበሬዎች ከይዞታቸው ይፈናቀላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአለም የምግብ ዋጋ ቢያሻቅብም እዚህ አገር ቤት ገዢዎቹ የህዝቡን ጉሮሮ በመዝጋት የእህል ዘርን ሁሉ በመግዛት ስለሚያከማቹ ኑሮ ለህዝቡ ምላጭ የሚያስውጥ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ትምህርት እጅግ በጣም አሰከፊ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ እንኳንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ሁተኛ ዲግሪም ይዞ አንብቦ የማይረዳው ቁጥሩ ቀላል አይደለም፡፡ መምህራንም ተማሪዎችም የወያኔ አባል መሆን ግዴታ ነው፡፡ ማንኛውም ሠራተኛ የወያኔ አባል መሆን የውዴታ ግዴታው ነው፡፡

በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየወረደ ያለውን ግፍ ለማስወገድና የዚህ ሁሉ ግፍ ምንጭ የሆነውን ወያኔን አሽቀንጥሮ ለመጣል ቃል ኪዳናችንን አድሰንና ወገባችንን ታጥቀን ከእግሮቻችን ላይ እሾህ አሜከላን ነቃቅለን ትግላችንን አጠንክረን እንገፋለን፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ድል ያደርጋል!
ኢህአፓ ያቸንፋል!